

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# ከጁላይ 1-31/2025 የነበረዉ የአየር ጠባይ ግምግማ እንዲሁም

# ከኦገስት 1-31/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ እና

# ምክረ ሃሳብ

ኦገስት 2025

አዲስ አበባ

ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## 1.1 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ጠባይ


ባለፈዉ የጁላይ ወር በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ በሰሜን እና መካከለኛዉ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን እና ክምችት ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ አና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በ 24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል አርባ ምንጭ 36.5፣ ባህርዳር 34፣ 62.3፣ 45.4፣ 32.2፣ ደብረ ማርቆስ 32.3፣ ኮምቦልቻ 39.6፣ ቢሾፍቱ 41.4፣ 37.7፣ ጎንደር 35.5፣ 39.7፣ ጎሬ 39.5፣ ጅማ 39.7፣ 51.5፣ መተሃራ 40፣ 35.7፣ ነቀምት 58.1፣ 35.8፣ 40.8፣ አቦምሳ 52.5፣ አቦቦ 37.6፣ አዲስ አበባ 35፣ አዴት 36፣ አይደር 31፣ አዲግራት 60.8፣ አይራ 32፣ 40.2፣ አማን 43.6፣ 65.6፣ 61.3፣ 41.6፣ አምቦ 34.5፣ አንግር ጉትን 30.2፣ 33.2፣ 39.4፣ 30፣ አሶሳ 54.6፣ አርጆ 34፣ 32.6፣ አዋሽ አርባ 78፣ አክሱም 38፣ አየሁ 36፣ አይከል 32.5፣ 31.4፣ 31.3፣ 31.6፣ በደሌ 39.4፣ 60.2፣ በሂ 34.3፣ ብላቴ 32.7፣ ቦሬ 30፣ ቡለን 39፣ 30፣ 34.5፣ ቻግኒ 50.6፣ ጭራ 50.2፣ 47.4፣ ዳንግላ 39.7፣ 31፣ ደብረ ብርሃን 35.5፣ 31.6፣ ደብረ ታቦር 30.4፣ 52.7፣ ደብረ ወርቅ 33.1፣ 34.1፣ ኢጃጂ 30.8፣ 40.2፣ እነዋሪ 36.3፣ ፊኙንዶ 30.6፣ 64.5፣ 38.2፣ ጋምቤላ 38.5፣ 39.2፣ 33.7፣ 30.5፣ 127፣ ወሊሶ 35.9፣ 43.6፣ ገዋኔ 52፣ ጊዳ አያና 38.1፣ 34.1፣ 49.8፣ 38.4፣ ጊምቢ 58.3፣ 31.3፣ 40.5፣ ጉንዶ መስቀል 36፣ 32.8፣ 42፣ 52.3፣ 54.7፣ ሆሳዕና 31፣ ቁሉምሳ 45.2፣ ካቺሴ 30.2፣ 33፣ ሊሙገነት 101፣ ማሻ 30.2፣ 40.4፣ 50.2፣ መተማ 37.4፣ ማይጨዉ 30፣ ማንኩሽ 46.6፣ ሞጣ 31.7፣ 32.1፣ 47.9፣ 39.6፣ ላሊበላ 34.4፣ መሃል ሜዳ 42.3፣ አዳማ 71.3፣ 44.3፣ 84.9፣ ንፋስ መወጪያ 32.8፣ 36.8፣ ኑራ ኤራ 34፣ 60.7፣ ፓዌ 31.5፣ 31፣ 32.1፣ 51.4፣ ሳውላ 34.5፣ ሰኮሩ 64.6፣ 30.6፣ ሰንቃጣ 34.2፣ 32.4፣ ሲሪንቃ 34.5፣ ሽሬ 40፣ ሻምቡ 38.8፣ ሾላ ገቢያ 50.5፣ 30፣ 36.6፣ ጽጺቃ 30.2፣ ተርጫ 45.6፣ ወገልጤና 37.1፣ ወረኢሉ 39.1፣ 42፣ ወላይታ 44.1፣ የትኖራ 47.3፣ 57.7፣ 30.8፣ አባይ ሸለቆ 32.3፣ 39.8፣ 31.2፣ 36.5፣ 36.4፣ 41.2፣ 37.8፣ 45.3፣ ኦቦሞሪንጋ 45.2፣ 65.2፣ አዲስ አለም 31፣ አዲስ ዘመን 33.2፣ አዲ አርቃይ 90፣ 95፣ 90.1፣ 98፣ 105፣ 80.4፣ 75.8፣ 77.7፣ 80፣ 81.5፣ 75.7፣ 75፣ 70፣ 72.5፣ 71.5፣ 72.8፣ አቃቂ 41፣ አሳሳ 30.5፣ 59፣ አታንጎ 36.5፣ 45.3፣ 48.6፣ አዋሮ መልካ 55.4፣ አዋሽ ሸለቆ 32.3፣ ቢላምቢሎ 63.7፣ ቡልቂ 31.5፣ ቡሬ 30፣ 30፣ ጨፌ ዶንሳ 67.3፣ ደራ 55፣ 40.5፣ 35.5፣ 35.5፣ 60፣ 70፣ 55.5፣ 30፣ 45፣ 32፣ 55.5፣ 40፣ 60.5፣ 45.5፣ 65፣ 75፣ 45.5፣ ደበረ ሲና 59.7፣ ደጋን 38.8፣ ደንገጎ 30.4፣ ፣ ዲንሾ 45.2፣ 41፣ እንዳ በጉና 39፣ ፈስ ቤት 35.9፣ 33.7፣ 38.1፣ 34.6፣ ፊንጫ 57.7፣

ጋሸና 37.2፣ 39፣ 106.9፣ 52.5፣ 61፣ 46፣ ጊናገረ 38.9፣ ጉብሬ 49.3፣ ጊሸ ራቢለ 66.7 ጉጉፈቱ 32.4፣ 36.8፣ 35.6፣ ሃይቅ 33.2፣ 40.5፣ ሃሮ 30.2፣ 30.4፣ 40፣ 30.2፣ 32.1፣50፣ 32.1፣ 30.2፣ 30፣ 50.1፣ 40.2፣ 30፣ ሀርዶዮ 48.5፣ ሁንቲ 32.5፣ ጅሁር 49.8፣ መንደዲ 64.8፣ 65.5፣114.8፣ ሰቆጣ 30.5፣ ከሚሴ 30.5፤ ቅዳሜ ገበያ 56.7 46.8፣ 36.7፣ 48.6፣ 56.8፣ ካራሚሌ 48፣ ኩሚ 80.4፣ 40፣ 33፣ ማርዬ 40.7፣ ማይሃነስ 64.6፣ መከነ እየሱስ 33.7፣ ሞላሌ 31.4፣ 36.3፣ ሙጊ 56.4፣ 32.7፣ ኖፓ 35፣ ኦሞ ናዳ 40.4፣ 37.6፣ 32.6፣ ኦንጋ 32፣ ሼንዲ 31.5፣ 53.5፣ 32.5፣ ሸበል በረንታ 35.6፣ ትንሹ ሚጢ 35.9፣ ዉቅሮ 36፣ 30፣ ዉልበርግ 53፣ያንፋ 39.7፣ 68፣ 57.5፣ 40.5፣ 59.9፣ ያዮ 41.3፣ 42.7፣ 36.1፣ ይርጋጨፌ 64፣ ዲክሲስ 33.2፣ ስሊጋ 39.4፣ መንደር አስራ አንድ 45፣ 82፣ 42፣ 38፣ 33.5፣ ስሊጋ 39.4፣ ደዊ 32.1፣ ሃረሲስ 35፣ ስልሳ 32.2፣ ተሩ 45፣ እንዲሁም ተላላቅ 36.2፣ 48.6፣ ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል።

በአጠቃላይ ባለፈዉ የጁላይ ወር በ137 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1)፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የምዕራብና የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 50.1-127 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ65 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካከል ጋምቤላ፣ መንዲዳ፣ ጋሸና፣ አዲዓርቃይ፣ አዳማ፣ መንደር አስራ አንድ፣ ኩሚ፣ አዋሽ አርባ፣ ደራ፣ ማይሃንሲ፣ ተርኮዲ፣ ያንፋ፣ ጨፌ ዶንሳ፣ ጊሸ ራቢለ፣ ኦቦ መሪንጋ ይገኙበታል (ምስል 1)፡፡





ምስል፡1 ከጁላይ 1-31 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ60 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው





ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

ባለፋዉ የጁላይ ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ አርሲ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ባሌ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሓረርጌ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ የመካከለኛዉ፣ የምዕራብና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ሰሜን፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ ዞኖች፣ የሰሜን ሸዋ ዞን፣ ዋግ ህምራ፣ የሰሜን እና የደቡብ ወሎ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺና መተከል ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ ምስራቅ፣ ደቡብ ምስራቅና ደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ ከአፋር ክልል የቀልበቲ፣ ሃሪ እና የጋቢ ዞኖች፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዠንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ፣ ወላይታ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ባስኬቶ ዞኖች፣ አዲስ አበባ ላይ ከ151-900 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ13-31 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡

ባለፈዉ የጁላይ ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፤ ምስራቅና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ከአማራ ክልል  ክልል የሰሜን፣ መካከለኛዉ፣ ምዕራብና ደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ሰሜን፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ አዊ፣ ዋግ ህምራ፣ ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ፣ ምምራቅ፣ ደቡብ ምስራቅና ደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ፣ ጋሞ፣ ወላይታና ባስኬቶ ዞኖች፣ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋና ሐረሪ ላይ በአብዛኛዉ ከመደበኛ ጋር የተቀራረበና በጥቂት ቦታዎች ላይ ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2025 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

በሌላ በኩል ኤሊዳር፣ ሰመራ፣ አዋሽ አርባ፣ ገዋኔ፣ አይሻ፣ መተሃራ፣ ዳሊፋጊ፣ ጎዴ፣ ጭፍራ፣ ድሬ ዳዋ፣ ሻዉራ፣ ቀበሪ ዳሀር፣ መተማ፣ መኢሶ፣ ጨፋ፣ ኑራ ኤራ፣ ጋምቤላ፣ አቦቦ፣ ባቲ፣ ሽርቆሌ፣ ፉኙዱ፣ ሻዉራ፣ ማሻ፣ አቦምሳ፣ ማጀቴ፣ ሲሪንቃ፣ ላሬ፣ ኮምቦልቻ፣ እና አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ 32.0 እስከ 45.8 ዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል፡፡

## 1.2 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባሳለፍነው የጁላይ ወር በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ከቦታ ቦታ በመጠን ይለያይ እንጂ በስርጭት ረገድ ብዙ ቦታዎችን ያደረሰ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸዉ፡፡ ይህም የተገኘው ዝናብ የአፈርን እርጥበት ከማሻሻልም አልፎ ከጁላይ ጀምሮ ለሚዘሩ የመኸር ሰብሎች ለመዝራትና አስቀድምው ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎች የውሃ ፍላጎታቸውን ከሟሟላት አንፃር የጎላ ሚና ከመኖሩም በላይ ከኤፕሪል ጀምሮ ቀደም ብለው ለተዘሩ እንደ በቆሎና ማሽላ ለመሳሰሉ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች እንዲሁም ለተለያዩ ቋሚ ተክሎች ለጓሮ አትክልቶችና ለፍራፍሬዎች በተሟላ ሁኔታ እንዲያድጉ የጎላ አስተዋፅዖ ነበረው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአርብቶ አደርና በከፊል የአርብቶ አደር አካባቢዎች የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት አዎንታዊ አስተዋፅዖ ነበረው፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ አካባቢዎች በተለይም ምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በሰሜን ምስራቅና በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረው ከፍተኛና ተከታታይነት ያለው እርጥበት ለጎርፍ መከሰትና በሰብል ማሳዎች ላይ የውሃ መተኛት ያስከተለ ሲሆን ይህም ሁኔታ እየተከናወነ በሚገኘው የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ ላይ በመጠኑም ቢሆን አሉታዊ ጎን ነበረው፡፡ በአንፃሩ በአንዳንድ አካባቢዎች ለመጥቀስም በደቡብ አሪ ወረዳ ከመር ቀበሌ በተከሰተው የመሬት ናዳ በሰው ህይወትና በንብረት ላይ ጉዳት አስከትሏል። በተጨማሪም በረዶ ቀላቅሎ ከጣለው ከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ በሰሜን ሸዋ በቅንብቢት እና በመሃል ሜዳ በሰብሎች ላይ ጉዳት እንዳደተረሰ መረጃዎች ያመለክታሉ (ካርታ 4 )።




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 1.3 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው ጁላይ ወር በአብዛኛው አባይ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ባሮ አኮቦ፣ ተከዜ፣ አዋሽ፣ ስምጥ ሸለቆ በላይኛው ገናሌ ዳዋ እና ዋቢ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የሆነ የገጸ ምደር የውኃ ፍሰት ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በላይኛው እና በመካከለኛው አባይ በጣም ከፍተኛ የሆነ የገጸ ምደር የውኃ ፍሰት ነበራቸው፡፡ ይህ ሁኔታ ለገፀ ምድር ውሃ መሻሻል ጥሩ አስተዋፅዖ እንደ ነበረው የተተነተኑ የውሃ የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በሌላ በኩል በወሩ ከነበረው ከፍተኛ የገጸ ምድር የውኃ ፍሰት ጋር ተያይዞ በኦሮሚያ፣ በጋምቤላ፣ ደቡብ ኢትዮጵያ፣ እንዲሁም በአዲስ አከባቢ በሸገር ከተሞች የተከሰተው ጎርፍ በመሰረተ ልማት እና በንብረት ላይ መጠኛ ጉዳት ጉዳት አድርሷል (ካርታ 5)።





ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2025
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 2 መግቢያ

በመደበኛ ሁኔታ የክረምት ዝናብ ቀደም ብሎ በደቡብ ምዕራብ እና በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚጀምር ሲሆን፤ በሂደትም እየተጠናከሩ ከሚሄዱ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ጋር ተያይዞ በኦገስት ወር ውስጥ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ሙሉ በሙሉ ዝናብ ያገኛሉ፡፡ የኦገስት ወር ከተቀሩት የክረምት ወራት በተሻለ ሁኔታ ሁሉንም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን አካቶ በመጠንም ሆነ በሥርጭት ከፍተኛ ደረጃ የሚደርስበት ወር ነው። ስለሆነም የወሩ አማካይ የዝናብ መጠን በምዕራብ አጋማሽ በአብዛኛው የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ ከ200-400 ሚ.ሜ እና በአንዳንድ ሥፍራዎች ላይ ከ400 ሚ.ሜ በላይ ይደርሳል። በእነዚህ አካባቢዎች የዝናብ ቀናትም በዚያው መልክ የሚጨምር በመሆኑ ከ18-30 ለሚደርሱት ቀናት ዝናብ ይኖራል። በሌላ በኩል በምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅ እና በመካከለኛው ኢትዮጵያ አካባቢዎች ላይም ቢሆን የዝናቡ መጠንና ሥርጭት እየተስፋፋ የሚሄድ በመሆኑ ከ6-20 ቀናት ያህል እስከ 300 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ በአማካይ ይኖራል። በመሆኑም የክረምቱ ዝናብ በስርጭትም ሆነ በመጠን በተሻላ ሁኔታ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን ላይ ከፍተኛ ጥንካሬ የሚያሳይበት ጊዜ ነው፡፡ በተለይም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ እና መካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ነጎድጓዳማ እና ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይዘወተራል፡፡


## 2.2 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በኦገስት የመጀመሪያው አስር ቀናት ለክረምት ዝናብ መፈጠር ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ይበልጥ እየተስፋፉና እየተጠናከሩ ይሄዳሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ መካከለኛው፣ ምስራቅ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6)። ስለሆነም እርጥበታማው የአየር ሁኔታ በተለይም በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ እና መካከለኛዉ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በሥርጭት እየተስፋፋ ከመሄዱ ጋር ተያይዞ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡ በተጨማሪም በደቡብ ምዕራብ፣ ሰሜን ምስራቅ፣ ምስራቅ እና በደቡብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡ በሌላ በኩል በመካከለኛው፣ በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል የሚችል ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 1-10, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

በሚቀጥሉት አስር ቀናቶች ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ብዙ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከመካከለኛ እስከ ከባድ (ከ11-30 ሚ.ሜ) መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በውሃ አካላትና በከባቢ አየር ውስጥ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በመካከለኛው፣ ደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 7)፡፡




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 1-10, 2025 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን


ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና በ24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን

| ክልል | ዞን | በ 24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን |
|---|---|---|
| አሮሚያ | የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ እና ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞኖች፣ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| | የምስራቅ ሸዋ፣ ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ምዕራብ ሐረርጌ፣ ምስራቅ ሐረርጌ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ እና ቦረና ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| አማራ | የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች | ከባድ መጠን (ከ30 ሚ.ሜ በላይ) |
| | የዋግ ህምራ፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ትግራይ | የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የመካከለኛዉ፣ የደቡብ ምስራቅ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |

| | | |
|---|---|---|
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ጋምቤላ | የአኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ በላይ) |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ሲዳማ ክልል | ሁሉም የክልሉ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ | | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| አፋር | የማሂ፣ ሀሪ፣ ቀልበቲ፣ ፈንቲ፣ አውሲ እና ጋቢ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | የወላይታ፣ ጎፋ እና ባስኬቶ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| | ጋሞ፣ ጌድዮ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| ሶማሌ | ሲቲ እና ፋፈን ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| | የኤረር፣ ጃረር፣ ነጎብ፣ ቆራሂ እና ዳዋ፣ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |

## 2.4 የሚኖረው የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት ሁኔታ

በኦገስት የመጀመሪያው አስር ቀናት ከሚኖረው የቀኑ ከፍተኛ የፀሐይ ሀይል ጋር በተያያዘ የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት በኤሊዳር፣ ዱብቲ፣ ሰመራ፣ ቡሬ፣ አሳይታ፣ ሁንዱፎ፣ ገዋኔ፣ ሚሌ፣ ዳሊፋጊ፣ አይሻ፣ ጉሊና፣ አዋሽ አርባ፣ ባቲ፣ ዶሎ ኦዶ፣ ዳዋ፣ ጎዴ፣ አቦቦ፣ ቋራ፣ አዋሽ ፈንታሌ፣ ጭፍራ፣ ላሬ፣ መተሃራ እና ፉኝዶ አከባበዎች ላይ ከ30.2 እስከ 38 ዲግሪ ሴልሺየስ እንደሚሆን አሃዛዊ ትንበያዎች ያመላክታሉ (ካርታ 8)፡፡




ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 1-10, 2025 የሚኖረዉ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

## 2.5 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በመደበኛ ሁኔታ በኦገስት ሁለተኛዉ አስር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በበለጠ ሁኔታ እየተጠናከሩ የሚሄዱበት ጊዜ ነው፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ በረዶ የቀላቀለ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ለወንዞች ሙላትና ለቅጽበታዊ ጎርፍ መከሰት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡

በመጪዎቹ የኦገስት ሁለተኛው አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚሁ ጋር በተያዘም በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ እና መካከለኛው የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር የአህዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም በሰሜን ምስራቅ እና ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡


## 2.6 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ

በመደበኛ ሁኔታ የኦገስት ወር ካለፉት የክረምት ወራት በተሻላ ሁኔታ ሁሉንም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን በመጠንም ሆነ በሥርጭት በከፍተኛ መጠን የሚያደርስበት ወር ነው፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ለተከታታይ ሰዓትና ቀናት የሚዘንብበትና በተጨማሪም በፀሐይ ሀይል ታግዘዉ ከሚፈጠሩ የደመና ክምችቶች በረዶ የቀላቀለ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ የሚስተዋልበት ሲሆን፤ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለወንዞች ሙላትና ቅጽበታዊ ጎርፍ የሚከሰትበት ወር ነዉ፡፡

በመጪው የኦገስት ወር ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች እየተጠናከሩ ሊሄዱ እንደሚችሉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ከሚጠናከሩት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ጋር ተያይዞ በተለይም በሰሜን ምስራቅ፣ በሰሜን፣ በመካከለኛዉ፣ በደቡብ ምዕራብና በምዕራብ የሃገሪቱ ቦታዎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ በፀሐይ ሀይል ታግዘዉ ከሚፈጠሩ የደመና ክምችቶች በመነሳት በረዶ የቀላቀለ እና ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል የሚችል ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥለዉ ወር ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም፣ ዋግ ህምራ፣ የሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፤ ከትግራይ ክልል ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ ፓዌ፤ አሶሳ፣ ካማሺ ዞኖች እና ማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ፤ ከጋምቤላ ክልል ንዌር፣ አኙዋክ፣ ማዣንግ እና የኢታንግ ልዩ ዞን፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋ እና ሐረሪ ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም ከዕለት ወደ ዕለት ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ገጽታዎች ላይ በመነሳት፣ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅና ምዕራብ ሀረርጌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፣ ምስራቅ ቦረና ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል ሲቲ፣ ፋፋን፣ ጀራር፣ ኤረር፣ ኖጎብ፣ ሊበን እና ዳዋ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ አውሲ፣ ጋቢ፣ ማሂ እና ሀሪ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ፣ ጋሞ፣

ጎፋ፣ ባስኬቶ፣ ጌድዮ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 9)፡፡




ካርታ 9 እ.ኤ.አ ከኦገስት1-31/ 2025 የሚኖረው የዝናብ መጠን

Ethiopian Meteorology Institute

## 2.7 እ.አ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው ወር ሰሜን ምስራቅ፣ ሰሜን፣ መካከለኛዉ፣ ደቡብ ምዕራብና ምዕራብ የሃገሪቱ ቦታዎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው እርጥበት ይኖራቸዋል፡፡ ይህም የሚኖረው እርጥበት በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለጓሮ አትክልቶችና ፍራፍሬዎች የዉሃ ፍላጎትን ለማሟላት እና በአሁኑ ጊዜ እርጥበት በማግኘት ላይ ለሚገኙት አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ዉሃ አቅርቦት ከማሻሻል አንፃር ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል።

በሌላም በኩል በአንዳንድ ቦታዎች ከሚኖረው ተደጋጋሚ የሆነ የእርጥበት መብዛት ጋር ተያይዞ በረባዳማ አካባቢዎች የውሃ በሰብል ላይ መተኛት፣ የመሬት አቀማመጡ ከፍታ ባላቸውና ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች ደግሞ የመሬት መንሸራተትና በጎርፍ የመጠቃት እንዲሁም እርጥበት በሚበዛባቸው አካባቢዎች የሰብል በሽታ እና የአረም መስፋፋት ሊከሰት ይችላል በመሆኑም አርሶ አደሮች እና ከፊል አርብቶ አደሮች እንዲሁም የሚመለከታቸው አካላት ሰብሎች በጎርፍ እንዳይጠቁ እና በማሳ ላይ ውሃ እንዳይተኛ የጎርፍ መቀልበሻዎችንና ከማሳ ውሰጥ ውሃን ማንጣፈፊያ ቦዮችን ማዘጋጀት እንዲሁም የፀረ-አረም እና የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በወቅቱና የአየር ሁኔታ ምቹነትን ባገናዘበ ሁኔታ ጥቅም ላይ ማዋል ያስፈልጋል፡

## 2.8 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ በውሃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በቀጣይ የኦገስት ወር በአብዛኛው አባይ፣ ተከዜ፣ ባሮ አኮቦ፣ አዋሽ፣ ኦሞ ጊቤ፣ አፋር ደናከል፣ መረብ ጋሽ፣ የላይኛው እና መካከለኛው ስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛው ዋቢ ሸበሌ እና በጥቂት የላይኛው ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከመካከለኛ እስከ እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም አልፎ አልፎ ከሚኖር ከባድ እና ተደጋጋሚ የዝናብ ሁኔታ ጋር ተያይዞ በተለይም ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ ተፋሰሶች እና ለጎረፍ መፈጠር አመቺ በሆኑ በአዲስ አባባ፣ ሀረር፣ ድሬ ዳዋ እና የኦሞራቴ ከተሞች ላይ ቅፅበታዊ ጎርፍ እና የወንዞች ሙላት የማስከተል አቅም ሊኖረው ይችላል። ስለዚህ ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ ወንዝ ዳርቻዎች፣ በረግረጋማ እንዲሁም ረባዳማ እና ተዳፋት አካባቢ በሚኖሩ ማህበረሰቦች በንብረት እንዲሁም በህይወት ላይ ጉዳት እንዳያስከትል ቅድመ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።